# የፍቅር አበባ

የፍቅር አበባ ካበረከትልሽ
እንሆ ቆሜአለሁ በጠዋት ከደጅሽ።
የነፍሴን ምኞት የልቤን ፍላጎት
ይህ ውብ ፅጌ-ረዳ ይገልጻል በማለት
ማልጄ ከእንቅልፌ ፈጥኜ ነቅቼ
ወደ አንቺ ገሰገስኩ አበባ ገዝቼ።
ይህንን አበባ እነሆ ተቀበይ
መውደዳችን ይጽና በአደባባይ ይታይ።
ይህ ውብ አበባ ጠውልጎ ቢደርቅም
እውነተኛ ፍቅር ይኖራል ዘለዓለም !
በልቤ ያለውን እውነተኛ ፍቅር
ልገልጽ በመፈለግ ለአንቺ በክብር
የፍቅር አበባ ይዤ ከደጃፍሽ
እነሆ ቆሜአለሁ ቆንጅት ደስ ይበልሽ።

"የእኔም እንባ ፈሰሰ"
ከተሰኘው በቅርቡ ለሕትመት ከሚውለው
የግጥም መድብል የተወሰደ

ደራሲ፥አስፋወሰን ዓለምሰገድ
ethioasfawose@yahoo.com
02/14/2009
©2010Asfawosen Alemseged